## የዋሽንግተን ግዛት (STATE OF WASHINGTON)
# DEPARTMENT OF CHILDREN, YOUTH, AND FAMILIES

1500 Jefferson Street, SE ● P.O. Box 40975 ● Olympia WA 98504-0975

ጁን 8፣ 2020
ለወላጆች ደብዳቤ

መጀመሪያ ይህንን ደብዳቤ በምታነቡበት ጊዜ እርስዎ እና ቤተሰብዎ ደህና እና ጤናማ እንደሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ እንደ እርስዎ ላሉት በህይወትዎ ውስጥ ታላላቅ ለውጦችን በማስተካከል ላይ ባለንበት ጊዜ ስላሳዩን ትዕግስ እና ስለተረዱን እናመሰግናለን፡፡ በእነዚህ አስቸጋሪ ጊዜያት የቤተሰቦችን ብሩህ አመለካከት፣ ቅልጥፍና እና ጥንካሬ እናደንቃለን። አንዳንዶቻችሁ ወደ ምናባዊ አገልግሎት መሸጋገርን ብታደንቁም በአካል በመገኘት የሚደረግ አገልግሎት መቅረቱ ለሌሎች አስቸጋሪ መሆኑን እንረዳለን፡፡

በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ በ COVID-19 የጊዜ ሂደት ላይ ተጽኖ በመኖሩ እና አገልግሎቶችን ለሚሰጡት ሕፃናት እና ቤተሰቦች ጤና እና ደህንነት ስጋት ላይ በመመርኮዝ Early Support for Infants and Toddlers (ESIT) የመንግስት መስሪያ ቤት ከተወሰኑ ግዴታዎች ጋር በአካል የሚደረግ አገልግሎቶች እንደተቋረጡ እንዲቀጥሉ ወስኗል፡፡

ወደ ምናባዊ አገልግሎቶች ለውጥ ያደረጋችሁ ብዙዎቻችሁ በአገልግሎቶቹ ቀላል ተደራሽነት እና በተሻሻሉ የአሰልጣኞች ስልጠና እንደተደሰታችሁ ሰምተናል፡፡ የምናባዊ አገልግሎቶችን ውጤታማነት የሚደግፍ ብዙ ምርምር አለ፤ እናም ይህ የአገልግሎት አሰጣጥ አቀራረብ እንደ አማራጭ ይቀጥላል።

በአካል ቀርበው እስኪሰጡ ድረስ አገልግሎቶችን ለመቀበል ለመቆየት የወሰኑ ወላጅ ከሆኑ፤ ምናባዊ አገልግሎቶችን እንዲሞክሩ እመክርዎታለሁ፡፡ *በልጅዎ ህይወት ፈጣን የእድገት ለውጥ ወቅት አስፈላጊው ጊዜ እንዳልባከነ እርግጠኛ እንዲሆኑ እንፈልጋለን።*
ሁሉም ፍላጎቶች በምናባዊ አገልግሎቶች በኩል ሊሟሉ እንደማይችሉ እናውቃለን፡፡ በተናጠል የ *ሁሉንም*) ህፃናት እና ቤተሰቦች ፍላጎቶችን ለሚሟላት በሰፊው የአካል አገልግሎቶች እስኪሰራጩ ድረስ የተለዩ በአካል አገልግሎቶች የጊዜ ወሰን የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት ለመለየት ስርዓት እየዘረጋን ነው፡፡ የልጆችን፣ የወላጆችን እና አገልግሎቱን የሚሰጡትን ሰራተኞች ደህንነት ባረጋገጠ መልኩ እንደዚህ ያሉ አገልግሎቶች የት እና እንዴት እንደሚቀርቡ እንወስናለን፡፡ ልጅዎ እነዚህን ውስን አካላዊ አገልግሎቶችን እንደሚፈልግ የሚያምኑ ከሆነ እባክዎን ሊኖርዎት ስለሚችል የጊዜ አመጣጥ እና አማራጮች ለመወያየት አገልግሎት ሰጪዎን ያነጋግሩ፡፡

አካላዊ አገልግሎቶች በደህንነት እንዲመለሱ የሚደረግ አቅድን ለማገዝ አገልግሎት ሰጪዎችን እና ቤተሰሰቦችን ያካተተ አናሳ የክንውን ቡድን ከ ESIT ከ Governor Inslee's Safe Start ጋር በመተባበር አቅድ ለማበልፀግ እየተገናኙ ነው፡፡

የዚህ ክንውን ቡድን ዓላማዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላል:

1. አጣዳፊ፣ የአጭር ጊዜ አካላዊ አገልግሎቶች ፍላጎት ያላቸውን አነስተኛ የጨቅላ ህፃናትና የታዳጊዎች ቡድን ልዩ ትኩረት ተግባራዊ እንዲሆን ጥቆማዎችን ማሳደግ::
2. ከ Governor Inslee's Safe Start Plan ጋር በመተባበር ክልላዊ አቀራረብን በመጠቀም አካላዊ አገልግሎቶችን የመመለስ የሽግግር እቅድን ማሳደግ፡፡

እቅዳችን ከመላው ግዛት የመጡ የ ESIT የአገልግሎት ሰጭዎች ከሁሉም በላይ ደግሞ የቤተሰቦች ግብረመልሶችን ያካትታል።

በጣም በቅርቡ ደግሞ በጣም አስቸጋሪ በሆነው በዚህ ወቅት የ ESIT አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ቤተሰቦች ተሞክሮ እና ተግዳሮቶች እንድንረዳ የሚያግዘንን የቤተሰብ የዳሰሳ ጥናት እናሰራጫለን፡፡

ለተግባራዊ ቡድን ሊያጋሯቸው የሚፈልጓቸው ጥያቄዎች፣ ስጋቶች ወይም ሀሳቦች ካሉዎት እባክዎን በ

laurie.thomas@dcyf.wa.gov ያግኙኝ፡፡

ይህንን አብረን በምናከናውንበት ወቅት ስለትዕግስትዎ አመስጋኞች ነን።

ከሠላምታ ጋር ፣

Laurie Thomas
አስተዳዳሪ
Early Support for Infants and Toddlers Program